


# ወደ ኖርዌይ መምጣት

# Coming to Norway


Aamiina
Julie Cornelia van Walsum
Loza Tadesse Mamo

5
አማርኛ am / English en




እኔና ሁለቱ ወንድሞቼ ወደ ኖርዌይ የመጣነው በታህሳስ 2016 ነው። በኖርዌይ ውስጥ እንደ ሶማሊያ ሞቃት ይሆናል ብለን ስላሰብን የበጋ ልብስ ለብሰን ነበር። ይሁን እንጂ አውሮፕላን ማረፊያው ስንደርስ በረዶ ነበር። በርዶን ነበር እና አየሩ ቀዝቃዛ ነበር። ጥቂት ሻንጣዎች ብናመጣም በውስጣቸው የበጋ ልብሶች ብቻ ነበሩ።

• • •

My two brothers and I came to Norway in December 2016. We wore summer clothes because we thought it would be as warm in Norway as it was in Somalia. However, when we arrived at the airport, it was snowing. We were cold and the weather was chilly. Although we had brought a few suitcases, they only had summer clothes in them.



ምንም እንኳን ቀዝቃዛ ቢሆንም ወደ ኖርዌይ ስንመጣ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። በስተመጨረሻ ለስድስት ዓመታት ያላየኋትን እናቴን እንደገና አገኘኋት። እናቴ እና ሁለት ጓደኞቿ አገኙኝ። ባየናት ጊዜ በደስታ አለቀስን። እማማ ወደምትኖርበት ትንሽ ከተማ በመኪናም ሄድን።

• • •

Even though it was cold, I was very happy when we came to Norway. I would finally meet my mum again, whom I had not seen for six years. My mum and two of her friends met us. When we saw her, we wept with joy. We drove to the small town where Mum lives.



የመጀመሪያዎቹ ቀናት እናቴ የምትኖርበትን ከተማ ለመልመድ ከባድ ነበር። ብርዳማ እና በረዶአማ ነበር በዛላይ ብዙም የሚታይ ነገር አልነበረም። መንገዶቹ ሙሉ በሙሉ ባዶ ነበሩ። ያገኘኋቸው ጥቂት ሰዎች ቀዝቃዛ እና የማይለመዱ ይመስሉ ነበር። በሶማሊያ በሁሉም ቦታ ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ ሁሉም ነገር እዚህ ያልተለመደ ሆኖ ተሰማኝ። እናቴ እና ጓደኞቿ አንዳንድ ስጦታዎች ሰጡን ከዚያም የክረምት ልብስ እንድንገዛ ወሰደችን።

• • •

The first days in Mum’s town were very strange. It was cold and snowy and there was not much to see. The streets were completely empty. The few people I met seemed cold and unfriendly. In Somalia there were people everywhere, so everything felt unfamiliar here. My mum and her friends gave us some presents, and then she took us to buy winter clothes.



ከገና በዓል በኋላ በጎልማሶች ትምህርት ማእከል የኖርዌይኛ ኮርስ ተቀላቀልኩ። እዚያም መደበኛ ትምህርት ቤት ከመጀመሬ በፊት ለሁለት ዓመታት አጠናሁ። አሁን የመጨረሻ አመት ላይ ነኝ። እና ብዙ አዳዲስ ጓደኞችን አፍርቻለሁ። እኔ በጣም ተግባቢ ነኝ። እና ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት ያዝናናኛል።

• • •

After the Christmas holidays I joined a Norwegian course at the adult education centre. I studied there for two years before starting in an ordinary school. Now I am in my final year, and I have made many new friends. I am very sociable and enjoy meeting other people.



ከትምህርት በኋላ በበጎ ፈቃደኞች ወደሚካሄደው ማእከል እሄዳለሁ። እዚያም በቤት ስራዎቼ ላይ እገዛ አገኛለሁ። በማዕከሉ የልብስ ስፌት ኮርስም ተቀላቅያለሁ።

• • •

After school I go to a centre run by volunteers where I get help with my homework. I have also joined a sewing course at the centre.



በሶማሊያ ከቁርኣን ትምህርት ቤት በቀር ተምሬም ሆነ ኮርስ ወስጄ አላውቅም። ማንበብና መጻፍ አላውቅም ነበር። አሁን በሶማሊኛ እና በኖርዌጂያን ቋንቋ እና ሌሎች በርካታ ትምህርቶችን እንዴት መጻፍ እንደሚቻል ተምሬያለሁ። በፊት ያለ ትምህርት ሰው እንዳልሆንኩ ይሰማኝ ነበር። አሁን ግን ደስተኛ እና ባለዕውቀት መሆኔ ይሰማኛል።

• • •

In Somalia I never went to school or did any courses except Quran school. I did not know how to read or write. Now I have learned how to write in both Somali and Norwegian, and many other subjects. Without education I felt I was nobody. Now I feel knowledgeable and happy.




በሚቀጥለው ዓመት በጤና እና በወጣቶች ልማት ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እጀምራለሁ። ወደፊት የወጣት ሰራተኛ መሆን እፈልጋለሁ። ትምህርቴን ስጨርስ ህልሜ ቋሚ ስራ ማግኘት ነው። እንዲሁም እንዴት መንዳት እንዳለብኝ መማር እና የመንጃ ፍቃድ ማግኘት እፈልጋለሁ።

• • •

Next year I will start secondary school in the health and youth development section. In the future I want to become a youth worker. When I have finished my education, my dream is to get a permanent job. I also want to learn how to drive and get my driver’s licence.



ሶማሊያ ብኖር ኖሮ አሁን እናት የምሆን ይመስለኛል። ምናልባት ብዙ ልጆች ይኖሩኝ ይሆናል። ሶማሊያ ብሆን ኖሮ አሁን ያገኘሁትን አይነት እድል አላገኝም ነበር። ኖርዌይ ውስጥ በመኖሬ እድለኛ ነኝ።

• • •

If I had stayed in Somalia, I think I would have been a mother by now. Perhaps I would already have many children. If I had been in Somalia, I would not have had the same opportunities as I have had now. I feel lucky to live in Norway.

# LIDA Stories

lidastories.net

## ወደ ኖርዌይ መምጣት

## Coming to Norway

Aamiina
Julie Cornelia van Walsum
Loza Tadesse Mamo (am)

CC BY